# Margins

**በካንሰሩ እጢ ዙርያ ያለው ቦታ**
**ከእጢው ጋር አብሮ ተቆርጦ የሚወጣው ቲሹ ነው**

እጢው ተቆርጦ ሲወጣ በእጥው አካባቢ ያለው ቲሹ አብሮ ይቆረጣል። እጢውና በአካባቢው ያለው ቲሹ በተለየ ቀለም ከተቀለመ በኋላ ከዚያ አካባቢ ውጭ ያለው ጠርዙ ወይም ማርጅኑ በአጉይ መነፀር ግልፅ ሆኖ ይታያል። ይህም ቲሹ በአጉይ መነፀር የሚታይበት ምክንያት በዚህ ጠርዝ ወይም ማርጅን አካባቢ ያለው ከካንሰር ሕዋስ ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። በዚህም አንፃር የእጢው ጠርዝ (Margin) ከዚህ በታች በተጠቀሰው ዓይነት ይብራራል።

ካንሰር-ገብ (Positive Margin) የካንሰሩ ሕዋሶች ከቀለመበት የቲሹው ሕዋስ አልፈዋል።

ካንሰር አልባ (Negative margin) የካንሰር ሕዋሶች በቀለመበት አካባቢ አልታዩም፣ (some negative margins are clean margins) ጥቂት ነጋቲቭ ማርጅኖች ንፁሕ ማርጂን ይባላሉ።

ካንሰር አልባ/ገብ (close margins) በካንሰር አልባና በካንሰር-ገብ መሐል ያለው ቦታ ተቀራራቢ ማርጂን ይባላል።

በእጢው አካባቢ ያለውን ከካንሰር ነፃ የሆነውን ቲሹ ቆርጦ ማውጣት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም ካንሰሩን በአጠቃላይ ለማስወገድ ይረዳል። ይህም (clearing the margins) ጠርዙን ማፅዳት ይባላል።

የካንሰሩ ሕዋሳት ለተቆረጠው ቲሹ ጠርዝ አካባቢ ባለው (edge) ምን ያህል ቅርበት እንዳለው ማወቅ ትክክል የሆነ ሕክምና ለመስጠት ይረዳል። በተለይም ይህ ሁኔታ በድጋሚ ቀዶ ጥገና ውሳኔ ለማድረግ ይረዳል። ወሰኑ (margin) ካንሰር-ገብ (positive) ከሆነ ተጨማሪ ቀዶ ጥገናዎች ያስፈልጋል ማለት ነው። የተጠጋ ካንሰር አልባ-ገብ ወሰን (close margins) ከሆነ ምናልባት ድጋሚ ቀዶ ጥገና ሊያስፈልግ ወይም ላያስፈልግ ይችላል ማለት ነው። ወሰኑ ካንሰር-አልባ (negative margins) ከሆነ ይህ ማለት ምናልባት ሌላ ተጨማሪ ቀዶ ጥገና አያስፈልግም ማለት ነው።

የካንሰር አልባ ወሰን (negative margins) በተለያዩ ሆስፒታሎች የተለያዮ ትርጉም ስላላቸው ይህን አስመልክቶ ሐኪምዎን በመጠየቅ የትኛው ወሰን ካንሰር-ገብ ፣ ካንሰር-አልባ ወይም ቀራቢ (close) መሆናቸው ከሐኪሙ መረዳት አልባ ሲል (negative) ምን ማለቱ እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው።